እንኳን ደህና መጣችሁ

የተጨማሪ ዕሴት ታክስ

2018

ሞጁል አራት

የተጨማሪ ዕሴት ታክስ

ክፍል አንድ

1. አጠቃላይ ሁኔታ

1.1. ዓላማ

1.1.1. ዋና ዓላማ፤

- ከሥልጠናው በኋላ ሠልጣኞች፡-
  - በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ መሠረት የሥልጠና ሞጁሉን ላይ ውይይት በማድረግ ስለተጨማሪ እሴት ታክስ ይረዳሉ።

1.1.2. ዝርዝር ዓላማ

- የተጨማሪ እሴት ታክስ ምንነት፣ ምዝገባ እና ስረዛ ይገልጻሉ፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ መጣኔዎች ያብራራሉ፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ስለማቀናነስ በምሳሌ ያስረዳሉ፤

ዝርዝር ዓላማ...

- የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ ስለማድረግ የሕግ አግባቡን በማስረዳት ተመላሽ የሚፈቀድባቸውን ግብይቶች ይለያሉ፤
- በገኘሀው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ ያስረዳሉ፤
- ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር የተያያዙ አስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች ይለያሉ።

1.3. ትርጓሜ

- **የግብዓት ታክስ** ፡-አንድን ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት በሚፈጸም ግዥ ላይ የሚከፈል የተጨማ ዕሴት ታክስ ነው፡፡
- **የምርት ውጤት ታክስ፡-** ምርት በሚሸጥበት /አገልግሎት በሚሰጥበት/ወቅት በመሸጫ ዋጋው ላይ ታስቦ የሚከፈል የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ነው፡፡

ትርጓሜ...

- **ተከፋይ ተጨማሪ ዕሴት ታክስ፡-** ግብር መክፈል ባለበት ሰው ለፌደራል አገር ውስጥ ገቢ ባስልጣን በታስ አዋጁ መሰረት የሚከፈል የተጨማ ዕሴት ታክስ ነው።
- **ዜሮ መጣኔ፡-** አቅርቦቱ ዜሮ ከመቶ የሚከፈልበት ሆኖ ነገር ግን ለአቅርቦቱ በግዥ ወቅት የተከፈለ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተመላሽ/ማካካሻ ሊጠየቅበት ይችላል።

❖ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ በአቅርቦት ሰንሰለት ደረጃዎች ላይ በሚፈጠር ዕሴት ወይም ከጥሬ አቅራቢው እስከ ቸርቻሪው ድረስ በሚኖረው የግብይት ሰንሰለት ወቅት በሚፈጠር እሴት ላይ የሚሰበሰብ እና የተንከባላይነት ባህሪ ያለው የታክስ አይነት ነው፡፡

ክፍል ሁለት

2.1. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምንነት

- የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ከሌሎች የታክስ አይነቶች አንጻር ሲታይ የቅርብ ጊዜ ታክስ ሲሆን እንደ ኢሮፒያን አቆጣጠር በ20ኛው ክፍለዘመን የመጀመሪያዎቹ አካባቢ (ከ1960 -1970ዎቹ) ባሉት ጊዚያት ውስጥ እንደተጀመረ ይነገራል፡፡

- የተጨማሪ ዕሴት ታክስ የራሱ የሆነ መጣኔ ያለው ሲሆን እንደየሀገሮቹ የኢኮኖሚ፤ የፖለቲካ እና የዕድገት ደረጃ የተለያየ ነው፡፡

የሀገራት ስም	ከፍተኛ የታክስ መጣኔ	የአገራት ስም	ዝቅተኛ የታክስ መጣኔ
ሀንጋሪ	27%	ኦማን	5%
ፊንላድ	25.5%	ዩናይትድ አረብ ኤምሬት	5%
ክሮሺያ	25%	ታይላንድ	7%
ኖርዌ	25%	ናይጀሪያ	7.5%
አይስ ላንድ	24%	ኮሪያ ሪፐብሊክ	10%
ግሪክ	24%	ሞንጎሊያ	10%
ፖላንድ	23%	ቬትናም	10%
ጣሊያን	22%	ካምቦዲያ	10%

2.3. የተጨማሪ እሴት ታክስ ጠቀሜታዎች

- በአገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች ከውጭ ከሚገቡ ምርቶች ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ይረዳል፣
- ለካፒታል ዕቃዎች የሚደረገው የታክስ ተመላሽ ኢንቨስትመንትን ያበረታታል።
- ወደ ውጭ በሚላኩ ምርቶች ላይ
  - ✓ ለግብዓቶች የተከፈለው ታክስም ተመላሽ የሚደረግ በመሆኑ

ጠቀሜታዎች…

- የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም በደረሰኝ ላይ ተመስርቶ የሚከናወን በመሆኑ
  - ✓ በቀላሉ ሳይከፈል ሊታለፍ ወይም
  - ✓ ሊጭበረበር የሚችል ታክስ ባለመሆኑ
  - ✓ የታክስ ስወራንና ማጭበርበርን በመቀነስ
  - ✓ በታክስ ሕግ አፈፃፀም ሊኖር የሚገባን ትክክለኛነትና ፍትሐዊነት በተሻለ አኳኋን ያስጠብቃል።

ጠቀሜታዎች…

- የተጨማሪ እሴት ታክስ ተግባራዊ በሚደረግበት ወቅት አነስተኛ ገቢ ባላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ሚዛናዊ ያልሆነ ጫና እንዳይፈጠር ለኑሮ መሠረታዊ የሆኑ የፍጆታ እቃዎችና አገልግሎቶች ከታክሱ ነፃ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

2.4. ታክሱ የሚጣልባቸው አቅርቦቶች (Taxable supplies)

- ታክሱ የሚጣለው በተመዘገበ ሰው የሚከናወን ማናቸውም ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ነው።
- ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ማለት ደግሞ
  - ✓ በህጉ ነፃ ከተደረጉት በስተቀር፤
  - ✓ ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት
  - ✓ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚቀርብ ዕቃ ወይም አገልግሎት ነው።

ታክሱ የሚጣልባቸው አቅርቦቶች...

- ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ተደርገው የሚቆጠሩ
  - የተመዘገበ ሰው ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የገዛቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለሌላ አገልግሎት እንዲውሉ ያደረገ እንደሆ፤
  - አሠሪው ለሠራተኞቹ በስጦታ ወይም በሌላ ማናቸውም አኳኋን የሚያቀርባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች፣
  - ምዝገባ ሲሰረዝ የካፒታል ዕቃዎችን ጨምሮ በተመዘገበው ሰው እጅ የሚገኙ ዕቃዎች፣
  - ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ አንድ ክፍል ሆኖ ተለይቶ በራሱ የሚንቀሳቀስ ክፍል የተሸጠ እንደሆነ፣

ታክሱ የሚጣልባቸው አቅርቦቶች...

ቅይጥ አቅርቦቶች

- አገልግሎትን ከማቅረብ ጋር በተያያዘ የሚከናወን የዕቃ አቅርቦት የአገልግሎት አቅርቦት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል።
- ከዕቃ አቅርቦት ጋር በተያያዘ የሚከናወን የአገልግሎት አቅርቦት የዕቃ አቅርቦት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል።
- አንድ አቅርቦት የዕቃ አቅርቦት እና የአገልግሎት አቅርቦት ከሆነ፣ የታክሱ ባለስልጣን ምክንያታዊ በሆነ መንገድ አቅርቦቱ የዕቃ አቅርቦት ወይም የአገልግሎት አቅርቦት ተደርጎ የሚወሰድበትን ሁኔታ በመመሪያ ይወስናል።

2.5. የታክሱ ከፋዮች

- የተመዘገበ ወይም መመዝገብ ያለበት ሰው፣
- ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባ
- ወደ አገር የሚገቡ አገልግሎቶችን በሚመለከት (በገዥው ስለሚሰበሰብ ታክስ)መሠረት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሆነ ሰው፣
- ለታክሱ የተመዘገበ ሰው ምዝገባው ከሚፀናበት ቀን ጀምሮ ታክስ ከፋይ ነው።
- መመዝገብ ያለበት ሆኖ ያልተመዘገበ ሰው ደግሞ የምዝገባ ግዴታ ከሚጀምርበት ጊዜ ቀጥሎ ያለው የሂሳብ ጊዜ ከሚጀምርበት አንስቶ ታክስ ከፋይ ነው።

ከታክሱ ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች እና መጣኔዎች

ነጻ የሆኑ አቅርቦቶች

- የተመረጡ የፋይናንስ አገልግሎት
- የህክምና ተቋም የሚሰጠው አገልግሎት
- የህክምና መሳሪያዎች እና መድሃኒቶች
- የሐይማኖት ነክ አገልግሎት
- ወርሃዊ ፍጆታ እስከ 200KWHመብራት እና 15 ሜትር ኩብ ውሃ

...ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች...

- ቢያንስ ሁለት ዓመት ያገለገለ መኖሪያ ቤት ሽያጭ እና የመኖሪያ ቤት ኪራይ፤
- ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ ማስገባት፣

- የበሰሉ ወይም የተዘጋጁ ምግቦች/መጠጦች
  - ✓ እንጀራ
  - ✓ ዳቦ እና ወተት

- የጸረ-ወባ ክትባት፣ ለህክምና ተቋማት የሚቀርብ ኦክሲጅን

...ነፃ የሆኑ አቅርቦቶች...

- የትምህርት ፕሮግራም
- በዓለም አቀፍ ስምምነት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነጻ የተደረጉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወደ ሀገር የሚያስገቧቸው ዕቃዎች
- ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች፣የኮንስላር ጽ/ቤቶች

2.7. የተጨማሪ እሴት ታክስ መጣኔዎች/Rates

- ሁለት የታክስ መጣኔዎች ይኖሩታል፡፡ እነሱም 15 ከመቶ መደበኛ መጣኔና ዜሮ ከመቶ መጣኔ (በታክስ መረብ ውስጥ የታቀፉ መሆናቸውን ለመግለጽ) የሚባሉት ናቸው፡፡

…መጣኔዎች…

- **15 በመቶ መጣኔ**

  - በተመዘገቡ ሰዎች የሚከናወን ታክስ የሚከፈልበት ግብይት፡-

    - "ታክስ የሚከፈልበት ግብይት" ማለት ከታክስ ነፃ ከተደረገው አቅርቦት በስተቀር ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት የሚከናወን ማናቸውም የዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች አቅርቦት ነው።

...መጣኔዎች...

- ✓ በተመዘገበ ሰው ስለሚከናወን ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የተቀመጠው መመዘኛ ባልተመዘገቡ ሰዎች የሚከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የተጨማሪ እሴት ታክስ እንደማይመለከተው ያመለክታል፣
- ✓ ሆኖም የተመዘገበ ሰው የንግድ ስራ ዕቃዎቹን ለግል ጥቅም ያዋላቸው ከሆነ የነዚህ ዕቃዎች አቅርቦት ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ እንዳዋላቸው ይቆጠራል፡፡

…መጣኔዎች…

❑ በዜሮ መጣኔ /0%/ ታክስ የሚከፈልባቸው

- ለውጭ የገበያ የሚቀርቡ ዕቃዎችና አገልግሎቶች (Exports)
- ዓለም አቀፍ የዕቃ ወይም የሰዎች የማጓጓዝ ተግባር፣ እንዲሁም በጉዞው አገልግሎት ላይ የሚውሉ የፍጆታ አቅርቦቶች
- ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ፣

…መጣኔዎች…

- ዜሮ ከመቶ መጣኔ /0%/ ታክስ ይከፈልባቸዋል ሲባል ከእነዚህ ግብይቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ አይሰበሰብም ማለት ነው፡፡

- አቅርቦቶቹ የሚቆጠሩት ታክስ እንደሚከፈልባቸው አቅርቦቶች (Taxable Suppiles) ሲሆን፣
- ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ በአጠቃላይ ዓመታዊ ሽያጭ ውስጥ ይታሰባሉ፡፡
- እነዚህን አቅርቦቶች የሚያመርትና አገልግሎት የሚሰጥ ሰው በግብዓት ላይ የከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማካካሻ/ተመላሽ ለማግኘት ይችላል፡፡

ክፍል ሦስት

3. የተጨማሪ ዕሴት ታክስ

3.1. የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባ

...ስለመመዝገብ...

➢ **የግደታ ምዝገባ**

✓ በማናቸውም የ12 ወራት ጊዜ መጀመሪያ በዚህ ሰው የሚከናወነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ጠቅላላ ድምር 2,000,000 ብር ሊበልጥ እንደሚችል የሚያሳምን ምክንያት ሲኖር፣

✓ በማናቸውም የ12 ወራት ጊዜ መጨረሻ ወይም ከዚህ ባነሰ ጊዜ ውስጥ በዚህ ሰው የተከናወነው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት 2,000,000 (ሁለት ሚሊዮን) ብር የጠቅላላ አቅርቦት ድምር ሲኖር በግዴታ ይመዘገባል

...ስለመመዝገብ...

- **[የፍቃደኝነት ምዝገባ]**

✓ በዓመቱ ያከናወነው ወይም ሊያከናውን የሚችለው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦቱ ዋጋ ከ1,000,000 (አንድ ሚሊዮን) ብር የሚበልጥ ከሆነ በፍቃደኝነት ሊመዘገብ ይችላል

- ✓ የተመዘገበ ሰው አንድ ምዝገባ ብቻ ያለው መሆኑ ግዴታውን በመወጣት ረገድ ከፍተኛ ጫና የሚያሳድርበት ከሆነ የቅርንጫፍ ምዝገባ እንዲፈቀድለት ሊያመለክት ይችላል፡፡
- ✓ ቅርንጫፉ፣የስራ ክፍሉ ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ ራሱን ችሎ እንዲመዘገብ የሚፈቀደው የታክሱ ባለስልጣን ለተመዘገበው ሰው በሚሰጠው የጽሑፍ ማስታወቂያ የተመለከቱ ሁኔታዎች እና ገደቦች እንደተጠበቁ ይሆናል፡፡
- ✓ በቅርንጫፎች እና በስራ ክፍሎች ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ የሚያከናውን ሰው መመዝገብ ያለበት በራሱ ስም እንጅ በቅርንጫፍ እና በስራ ክፍሎች ስም ሊሆን አይችልም

- ✓ ተለይቶ የተመዘገበ ቅርንጫፍ፤ የስራ ክፍል ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ለዋናው መስሪያ ቤት ወይም ለሌላ ተለይቶ ለተመዘገበ ቅርንጫፍ የሚያቀርበው አቅርቦት ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የተፈጸመ አቅርቦት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል።
- ✓ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታን ለሚያስከትለው የግብይት መጠን አፈጻጸም እያንዳንዱ ተለይቶ የተመዘገበ የአንድ ኩባንያ ቅርንጫፍ፤ የስራ ክፍል፤ ወይም የተለየ ታክስ የሚከፈልበት የስራ እንቅስቃሴ ግብይት የኩባንያው አቅርቦት ውስጥ ይደመራል።
- ✓ የታክሱ ባለስልጣን የሚደረገውን የግብአት ተቀናሽ በቅርንጫፍ ደረጃ ሳይሆን በተመዘገበው ሰው ዋና መስሪያቤት ደረጃ እንዲፈጸም ሊያዝ ይችላል

- ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ በሚያካሂድበት ዋነኛ የስራ ቦታ በግልጽ በሚታይ ስፍራ ዋናውን የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባ የምስክር ወረቀት የመለጠፍ፤
- የተሠጠውን የተጨማሪ ዕሴት ታክስ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ቅጂ ታክስ የሚከፈልበት እንቅስቃሴ በሚያካሂድባቸው ሌሎች የስራ ቦታዎች ሁሉ በግልጽ በሚታይ ሥፍራ የመለጠፍ ግዴታ አለበት።

የተመዘገበ ሰው ግዴታዎች

- የተመዘገበ ሰው ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበበትን ዝርዝር መረጃ ታክስ የሚከልበትን ስራ በሚያከናውንበት ዌብሳይት እና የማህበራዊ ሚዲያ አድራሻ ላይ ማስፈር አለበት።
- የተመዘገበ ሰው ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበበትን ዝርዝር መረጃ ታክስ የሚከልበትን ስራ በሚያከናውንበት ዌብሳይት እና የማህበራዊ ሚዲያ አድራሻ ላይ ማስፈር አለበት።

ክፍል አራት

4. የተጨማሪ እሴት ታክስ ማቀናነስ እና ተመላሽ

...ስለማቀናነስ...

4.1 ማቀናነስ

- አንድ ሰው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገበ ከሆን
  - ለንግድ ሥራው ባከናወናቸው ግዥዎችና ወጪዎች ላይ ለከፈለው የግብዓት ተጨማሪ እሴት ታክስ ማካካሻ ሊጠይቅ /ሊያስብ/ ይችላል፡፡
- የግብዓት ታክስ የምንለው፤- በጥሬ ዕቃዎች ግዢ ወይም ዕቃዎችን መልሶ ለመሸጥ በተደረገ ግዢ ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብቻ ሳይሆን የሚከተሉትንም ይጨምራል፡፡

...ስለማቀናነስ...

1) ለንግድ ሥራው የተገዙ የቢሮ ዕቃዎችን፣
2) ከንግድ ሥራው ጋር በተያያዘ ለዕቃ ማጓጓዣ የተገዙ ተሽከርካሪዎችን፣
3) ለንግድ ሥራው ተግባር የዋሉ የቴሌፎን ወጪዎችን፣
4) ከንግድ ሥራው ጋር በተያያዘ ለጠበቆች ወይም ለአካውንታንቶች ለተፈፀሙ ክፍያዎች ወዘተ...

...ስለማቀናነስ...

- ታክስ ለሚከፈልበት የንግድ ሥራ የዋሉ ቢሆንም ግብዓቶቹ ሲገዙ የተከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማካካስ /ተመላሽ መጠየቅ አይቻልም፡፡

1. ለመንገደኛ ማጓጓዝ ተሽከርካሪዎች የተከፈለ፡-

- የንግድ ሥራው በነዚህ ተሽከርካሪዎች ንግድ/ሽያጭ ወይም ኪራይ የተሠማራ ካልሆነ በስተቀር፣

2. መንገደኛ ማጓጓዝ ተሽከርካሪዎች ዕድሳትና ጥገና የተከፈለ፡-

  - ✓ የንግዱ ሥራ ከነዚሁ ተሽከርካሪዎች ጋር የተቆራኘ ወይም
  - ✓ ተሽከርካሪዎቹን ማከራየት እስካልሆነ ድረስ፣

...ስለማቀናነስ...

3. ለመዝናኛ የተከፈለ ወጪ፡-

- ✓ የንግድ ሥራው የመዝናኛ አገልግሎት አቅራቢ እስካልሆነ ድረስ፣
- ✓ ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፈለበት የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት የንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ከሆነ እና
- ✓ የመዝናኛው አገልግሎት ለመንገደኞች የሚሰጥ የትራንስፖርት አካል ሲሆን፣የታክስ ተቀናሽ አይከለከልም፡፡(አየር መንገድ፣....)

...ስለማቀናነስ...

- አዲስ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ተቀናሽ የሚደረገው ግዥ የተፈጸመው፡-

  የንግድ ዕቃዎችን በሚመለከት፣ ከተመዘገበበት ቀን በፊት ባለው የ6 ወር ጊዜ ውስጥ ከሆነ፣

- የካፒታል ዕቃዎችን በሚመለከት፣ ከተመዘገበበት ቀን በፊት ባለው የ3 ዓመት ጊዜ ውስጥ ከሆነ፣ እና

- የተመዘገበው ሰው የታክሱን ባለስልጣን በሚያረካ አኳኋን ተቀናሽ ለሚደረገው ግዥ የግብአት ታክስ የከፈለ መሆኑን እና የከፈለውን ታክስ መጠን የሚያሳይ የታክስ ደረሰኝ ወይም ሌላ የሰነድ ማስረጃ ካቀረበ::

...ስለማቀናነስ...

- የግብአት ታክስ ተቀናሹ የተመዘገበው ሰው ከተመዘገበበት ቀን ቀጥሎ ባለው የመጀመሪያ የሂሳብ ጊዜ መቅረብ አለበት፡፡
- የንግድ እቃዎችን በተመለከተ የተመዘገበው ሰው የግብአት ታክስ ተቀናሽ ማግኘት የሚችለው በተመዘገበበት ቀን በእጁ የሚገኙ የንግድ ዕቃዎችን በገዛበት ጊዜ ለከፈለው የግብአት ታክስ ይሆናል፡፡

❑ታክስ የሚከፈልባቸውን እና ከታክስ ነፃ ለሆኑ አቅርቦቶች ግብዓትን መጠቀም

- እነዚህ ግብዓቶች በቀጥታ ታክስ ለሚከፈልባቸው አቅረቦቶች የዋሉ ከሆነ የግብዓቶቹ ላይ የተከፈሉት ታክሶች በጠቅላላው ተቀናሽ ይደረጋሉ፣
- ግብዓቶቹ በቀጥታ ከታክስ ነፃ ለሆኑ አቅርቦቶች የዋሉ ከሆነ በግብዓቶቹ ላይ የተከፈሉ ታክሶች ተቀናሽ አይደረጉም፣

…ስለማቀናነስ…

- ግብዓቶቹ ለሁለቱም አቅርቦቶች(ታክስ የሚከፈልባቸውን እና ከታክስ ነፃ የሆኑ) የዋሉ ሲሆን ተቀናሽ የሚደረገው የታክስ ድርሻ (95%፡5%) መጠን ይወሰናል።
- የተመዘገበ ሰው በአንድ የታክስ ዘመን ውስጥ እንዲቀናነስለት ሊደረግ የሚችለው የታክስ መጠን ድምር በዚሁ የታክስ ዘመን ውስጥ ባከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ የበለጠ እንደሆነ በብልጫ የሚፈፀም ይሆናል።

...ስለማቀናነስ...

- ለታክሱ የተመዘገቡ ሰዎች በአንድ የሂሳብ ጊዜ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ በላይ ተቀናሽ እንዲደረግ የተጠየቀው ታክስ ለቀጣዮቹ 6 (ስድስት) የሂሳብ ጊዜዎች እንዲተላለፍ ሆኖ በእነዚህ ጊዜዎች ከሚደረግ ክፍያ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል።
- ይህ የስድስት ወር ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ቀሪ ሂሳብ ቢኖር የተመዘገበው ሰው በብልጫ የተከፈለውን ታክስ ከሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ ጋር በማያያዝ ጥያቄውን ባቀረበ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ባለስልጣኑ ሂሳቡን ተመላሽ ያደርጋል።

- በእያንዳንዱ ታክስ የሚከፈልበት ጨዋታ ሳይሆን በእያንዳንዱ የሒሣብ ጊዜ ውስጥ ካከናወነው ጨዋታ በሚገኘው ትርፍ ላይ በመመስረት ይሰላል፡፡
- በአንድ የሂሳብ ጊዜ ሊኖረው የሚገባው የውጤት ታክስ
- **(ሀ-ለ) x ሐ**
- ሀ” ማለት፡- በሂሳብ ጊዜው ውስጥ የእድል ሙከራ የተደረገበት ጠቅላላ የገንዘብ መጠን፤
- “ለ” ማለት፡- በሂሳብ ጊዜው ውስጥ የተሰጠው ሽልማት የገንዘብ ዋጋ፤
- “ሐ” ማለት የታክስ ክፍልፋይ፤ (15%)

- **ምሳሌ፡-** በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ የዕድል ሙከራ የተደረገበት ጠቅላላ የገንዘብ መጠን 5,000,000 ቢሆን እና የተሰጠው የሽልማት መጠን ደግሞ 1,000,000 ቢሆን
- (ሀ-ለ)*ሐ
- በዚህ መሰረት (ሀ)= 5000,000 (ለ)= 1000,000 (ሐ)=የታክስ ክፍልፋይ ነው። በዚህ መሰረት (ሀ-ለ)*ሐ በተሰጠው ቁጥር ተክተን ውጤቱን እናገኛለን ይህም እንደሚከተለው ይሆናል።
- (5000000-1000000)*15/115 = 4,000,000*15/115 = **<u>521,739.1</u>** የውጤት ታክስ ሆኖ የሚወሰደው

❖ የመድን አገልግሎት በሁለት ይከፈላል

1. **የህይወት መድን፡-** ሞት እና የአካል ጉዳት የመሳሰሉት ከታክሱ ነጻ ተደርገዋል
2. **ጠቅላላ መድን**

➢ የመድን ሰጪ ድርጅት የሚያቀርበው የጠቅላላ መድን ውል አቅርቦት የተጨማሪ እሴት ታክስ ተፈፃሚ ይሆንበታል፡፡

➢ የውሉ አካል ቢሆንም ባይሆንም የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት በደረሰ ጉዳት ምክንያት የጠቅላላ መድን ካሣ የተቀበለ እንደሆነ የዚህ ዓይነቱ ክፍያ የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን የሥራ እንቅስቃሴ በማከናወን ሂደት ለአገልግሎቱ አቅርቦት እንደተከፈለው ዋጋ ይቆጠራል፡፡ይህ ተፈፃሚ የሚሆነው ለታክሱ ለተመዘገበ ሰው በሚከፈለው የመድን ካሳ ክፍያ ላይ ብቻ ነው፡፡

- የአቅርቦቱ ዋጋ ነው የሚባለው የተመዘገበው ሰው ከተቀበለው ገንዘብ ላይ የታክሱ ክፍልፋይ የገንዘብ መጠን ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ሒሣብ ነው።

- ምሳሌ፡- ለካሳ የተከፈለው ጠቅላላ አቅርቦት 1,150,000 ብር ቢሆን ይህንን በታክሱ ክፍልፋይ አባዝተን የተገኘውን ውጤት ከ 1,150,000 ላይ በመቀነስ የአቅርቦቱን ዋጋ እናገኛለን

- <u>በዚህም መሰረት፡-</u>

- ሀ/(100+ሀ)= 15%/(100+15%) =15/115* 1,150,000 = 1,150,000 -150,000 =1000,000

- በዚህም መሰረት የአቅርቦቱ ዋጋ 1,000,000 ብር ሲሆን ታክሱ 150,000 ይሆናል ማለት ነው።

- አቅርቦቱ ወይም ወደ ሀገር የማስገባቱ ተግባር በተከናወነበት ጊዜ ግዢው የተፈጸመው ታክስ ለሚከፈልበት አቅርቦት መሆኑ ለተረጋገጠ ተቀናሽ ለሚደረግ ግዥ የተመዘገበ ሰው የከፈለው የግብአት ታክስ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡
- የተጨማሪ ዕሴት ታክስ በባህሪው በግዥ (ግብዓት) ላይ የተከፈለን ታክስ በሽያጭ (በውጤት) ላይ ከተከፈለው ታክስ የማቀናነስ እና የተንከባላይነት ባህሪ ያለው ነው፡፡

የንግድ ስራዎች	ግዥ	ሽያጭ	የግብዓት ታክስ	የሽያጭ ታክስ	ተከፋይ ታክስ
ቢ.ፒ.ኤን እንጨት አቅራቢ	0	500,000	0	75,000	75,000
ኤፍ.አር.ኤስ ጣውላና ኤምዲኤፍ አቅራቢ	500,000	1,000,000	75,000	150,000	75,000
ጂ.ኤም.ሲ ፈርኒቸር	1,000,000	2,000,000	150,000	300,000	150,000
ኤም.ኦ.አር የእንጨት ስራ ውጤቶች ቸርቻሪ	2,000,000	3,000,000	300,000	450,000	150,000
አጠቃላይ					450,000

- **<u>ምሳሌ፡-</u>** ሐበሻ ቢራ አክሲዮን ማህበር ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ድርጅት ሲሆን በህምሌ 2017 ዓ.ም የቢራ ሽያጭ 500,000 ዋጋው ተጨማሪ እሴት ታክስን ሳይጨምር በብር 66 ነው። ድርጅቱ 500 ኩንታል የቢራ ብቅል ዋጋው ተጨማሪ እሴት ታክስን ሳይጨምር በኩንታል 2000 ብር ከአርሲ ብቅል ፋብሪካ (ለተ.እ.ታ የተመዘገበ) በዚሁ ወር ግዥ ፈፅሟል።

- ➢ በተጨማሪም አክሲዮን ማህበሩ ለቢራ ማምረቻ የሚሆኑ ኬሚካሎችንና ሎሌች ጥሬ ዕቃዎችን ከተጨማሪ ዕሴት ታክስ ውጭ በብር 100,000 (የዕቃው ዋጋ፣ኢንሹራንስ እና ሌሎች ቀረጦችን ጨምሮ) በዛው በተመሳሳይ የታክስ ወር ከውጭ አስገብቷል፡፡

- ✓ የተጠየቀ፡- የተጠቀሰው ወር የግብዓት ታክስ አቀናንስ?

...ስለማቀናነስ...

- **መልስ፡**

- የምርት ውጤት ታክስ: 500,000 x 66 x 15%,= 4950000

- ሲቀነስ የተከፈለ የግብዓት ታክስ :

- ብቅል፡- 500 x 2000 x 15%= 150,000.00
- [illegible] 100,000x15%=15,000.00

...ስለማቀናነስ...

- በዚህም መሰረት

> ➢ ተከፋይ ታክስ = የምርት ውጤት ታስ <u>ሲቀነስ</u> የግብዓ ታክስ፡4950000-165,000 = 4785000<u>.00 ብር</u>

ሙከራ ሁለት

1. የተጨማሪ እሴት ታክስ ስለማቀናነስ በምሳሌ አስረዱ?

- የግብዓት ታክስ ከውጤት ታክስ ከበለጠ" ከግብዓት ታክስ ላይ የውጤት ታክስን በመቀነስ የተገኘው የገንዘብ መጠን ወደፊት እንዲሸጋገር ተደርጎ የሚቀጥለው የሒሣብ ጊዜ የተመዘገበው ሰው የግብአት ታክስ ሆኖ ተቀናሽ ይደረጋል
- የተመዘገበ ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ውስጥ ያለው በብልጫ የከፈለው ታክስ ለስድስት የሒሣብ ጊዜ ያህል የተሸጋገረ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ያልተደረገ ከሆነ፣ ተቀናሽ ያላደረገው የገንዘብ መጠን ተመላሽ እንዲደረግለት ለታክሱ ባለሥልጣን ሊያመለክት ይችላል፡፡

- የተመዘገበ ሰው የሚያቀርበው የተመላሽ ጥያቄ ስድስተኛው የሒሣብ ጊዜ በተጠናቀቀ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡ በዚሁ መሰረት ጥያቄውን ካላቀረበ ተመላሽ የማግኘት መብቱን እንደተወ ይቆጠራል፡፡
- የተመዘገበው ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ካከናወነው አቅርቦት ዋጋ ውስጥ አምሳ በመቶ (50%) ወይም ከዚያ በላይ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚደረግበት ከሆነ ታክስ ካስታወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የታክሱ ባለሥልጣን በሒሣብ ጊዜው በብልጫ የተከፈለውን የግብአት ታክስ ተመላሽ ማድረግ አለበት፡፡

- የተመዘገበው ሰው በአንድ የሒሣብ ጊዜ ካከናወነው አቅርቦት ዋጋ ውስጥ አምሳ በመቶ (50%) ወይም ከዚያ በላይ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚደረግበት ከሆነ ታክስ ካስታወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የታክሱ ባለሥልጣን በሒሣብ ጊዜው በብልጫ የተከፈለውን የግብአት ታክስ ተመላሽ ማድረግ አለበት።
- የተመዘገበው ሰው የካፒታል ዕቃው ለተገዛበት የሂሳብ ጊዜ ተመላሽ እንዲፈቀድለት ማመልከቻ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመላሽ የሚደረግለት ከታች የተዘረዘሩት ሲሟሉ ነው።

- ዓመታዊው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦቱ ከብር 100 ሚሊዮን ብር በላይ የሆነ የተመዘገበ ሰው ተቀናሽ የሚደረግ የካፒታል ዕቃዎች ግዢ የፈጸመ እንደሆነ
- የተመዘገበው ሰው ተቀናሽ ለሚደረገው የካፒታል ዕቃዎች ግዢ የግብዓት ታክስ ተቀናሽ የማግኘት መብት ያለው ከሆነ
- ተቀናሽ የሚደረገው ግዥ በተከናወነበት የሒሣብ ጊዜ የግብዓት ታክሱ የገንዘብ መጠን ሙሉ በሙሉ ተቀናሽ ያልተደረገ ከሆነ።
- የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባው የተሰረዘ ሰው ተቀናሽ ያልተደረገ የግብዓት ታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት የሚያቀርበው ማመልከቻ በበቂ ማስረጃ የተደገፈ ከሆነ ማመልከቻው በቀረበለት በስልሳ (60) ቀን ጊዜ ውስጥ ተመላሹ ይከፈለዋል።

- ምዝገባው በተሰረዘበት እለት ተቀናሽ ያልተደረገ የግብአት ታክስ ያለው ሰው ተቀናሽ ያልተደረገው የግብአት ታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት ማመልከቻ ያላቀረበ እንደሆነ መብቱ የሚቋረጥ ሲሆን፤ ተቀናሽ ያልተደረገው የግብአት ታክስ ተመላሽ ሊደረግለት አይችልም።

....ተመለሽ....

- ምሳሌ፡-ጊዮን ጫማ ፋብሪካ ለተ.እ.ታ ተመዝጋቢ ሲሆን 10,000 ኪ.ግ ቆዳ ከአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ (ለተ.እ.ታ ተመዝጋቢ) ቫትን ጨምሮ በኪሎ 690 ብር ገዛ ።በተጨማሪም ለጫማ ምርት የሚሆን ኬሚካል እና ሌሎች ጥሬ ዕቃዎች በብር 400,000 (C.I.F እና ሌሎች ቀረጦች ቫትን ሳይጨምር) ለህዳር ወር ምርት የሚሆን ከውጭ አስገብቷል። ጊዮን ፋብሪካ ደረጃውን የጠበቀ የ 3 ሚሊዮን ብር ዋጋ ያለው ጫማ ወደ ካናዳ እና ህንድ በመላክ የሸጠሲሆን እንዲሁም 20,000 ጫማ ቫትን ሳይጨምር በጫማ 300 ብር ለሀገር ውስጥ ገበያ ሸጠ።

....ተመለሽ....

- **<u>ጥያቄ፣-</u>** የወሩን ቫት አቀናነስ
- **<u>መልስ</u>**

ሀ. የምርት ውጤት ታክስ

ለ. ወደአገር ውሥት የገባ 20,000x300x15%

900,000.00

ሐ. ወደውጭ የተላከ፣ 3,000,000x0%

መ. ሲቀነስ: ለግብአት የተከፈለታክስ :

....ተመላሽ....

ሌዘር 10,000x690x15/115 900,000.00

ኬሚካል 400,000x15/100 60,000.00

አጠቃላይ የተከፈለ የግብዓት ታክስ ፡

960,000.00

ተመላሽ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ፡
60,000.00

....ተመላሽ....

- ተመላሽ የተጨማሪ ዕሴት ታስ = የምርት ውጤት ታክስ - የግብአት ታክስ

- ከላይ እንደተገለፀው 60,000.00 ብር በአብላጫ የተከፈለ የግብዓት ታክስ የወሩ ክሬዲት ሲሆን እስከሚቀጥለው 6 ተከታታይ ወር ማቀናነስ የሚችል ሲሆን 6 ወራት ውስት ካልተጣፋ ግን ጊዮን ጫማ ፋብሪካ ተመላሽ ጠይቆ በባለስልጣኑ ይመለስለታል።

- ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት የሚያከናውን የተመዘገበ ሰው አቅርቦቱን ባከናወነበት ጊዜ አቅርቦቱን ለገዛው ሰው መደበኛውን የታክስ ደረሰኝ መስጠት አለበት፡፡
- በቀጥታ በገዢው ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው አገልግሎቱን ባገኘበት ጊዜ ለአቅርቦቱ በገዢው የሚዘጋጅ የታክስ ደረሰኝ ማዘጋጀት አለበት፡፡
- የተመዘገበ ሰው ለአንድ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ሊሰጥ የሚችለው አንድ ደረሰኝ ብቻ ነው፡፡

- ማስተካከያ ማድረግ የሚያስገድድ ሁኔታ ሲፈጠር ሊሰጥ የሚችለው አንድ የክሬዲት ሰነድ ወይም አንድ የዴቤት ሰነድ ነው።

- የተመዘገበ ሰው የሚከተሉትን ሰነዶች መያዝ አለበት።
  - ✓ የተቀበላቸውን ዋንኛ የታክስ ደረሰኞች፣ የክሬዲት ሰነዶች እና የዴቢት ሰነዶች በሙሉ፣
  - ✓ የሰጣቸውን የታክስ ደረሰኞች፣ የክሬዲት ሰነዶች እና የዴቢት ሰነዶች ቅጂዎች በሙሉ፤
  - ✓ ወደ ሀገር ካስገባቸው ወይም ወደ ውጭ ከላካቸው ዕቃዎች ጋር የተያያዙ የጉምሩክ ሰነዶች
  - ✓ የአገልግሎቱ ተቀባይ በሆነ የተመዘገበ ሰው የተዘጋጁ ከሆነ ይህ ሰው በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት የሚመለከቱ የታክስ ደረሰኞች።

የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ማሳወቅ

- ማናቸውም የተመዘገበ ሰው የእያንዳንዱን የሒሣብ ጊዜ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ የሒሣብ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኋላ ቀጥሎ ባለው ወር የመጨረሻ ቀን ድረስ ማቅረብ አለበት፡፡
- ማናቸውም የተመዘገበ ሰው በሒሣብ ጊዜው ውስጥ ተከፋይ የሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ቢኖረውም ባይኖረውም የሒሣብ ጊዜውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታ አለበት
- የተመዘገበ ሰው በሒሣብ ጊዜው የሚኖረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ የተጣራ ሒሣብ ታክሱን ሊያስታወቅ በሚገባው ጊዜ ውስጥ መክፈል አለበት፡፡
- የተመዘገበ ሰው በሒሣብ ጊዜው የሚኖረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ የተጣራ ሒሣብ ታክሱን ሊያስታወቅ በሚገባው ጊዜ ውስጥ መክፈል አለበት፡፡

የተጨማሪ ዕሴት…

- የተመዘገበ ሰው በሒሣብ ጊዜው የሚኖረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ የተጣራ ሒሣብ ታክሱን ሊያስታወቅ በሚገባው ጊዜ ውስጥ መክፈል አለበት፡፡
- የተመዘገበ ሰው በሒሣብ ጊዜው የሚኖረውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ የተጣራ ሒሣብ ታክሱን ሊያስታወቅ በሚገባው ጊዜ ውስጥ መክፈል አለበት፡፡

- በቀጥታ በገዢው ታክስ በሚከፈልበት አቅርቦት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ከፍተኛ ግብይት ያለው ያልተመዘገበ ሰው ወይም ያልተመዘገበ የመንግሥት ተቋም ግብይት ለፈጸመበት ወር ግብይቱ በተፈጸመ በሚቀጥለው ወር የመጨረሻ ቀን ለታክሱ ባለስልጣን የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ አለበት፡፡
- የተመዘገበ የውጭ አቅራቢ በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ከሂሳብ ጊዜው ቀጥሎ ባለው ወር የመጨረሻ ቀን ወይም ከዚያ በፊት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ አለበት፡፡

በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ

- ማናኛውም ወኪል ለአቅራቢው መክፈል ካለበት ታክስ ውስጥ 50% ቀንሶ በመያዝ ለገቢ መስሪያ ቤቱ ገቢ ማደረግ አለበት፡፡
- ቀሪውን 50 % ለአገልግሎት አቅራቢው መከፈል አለበት፡፡
- ከዕቃ/የአገልግሎት ክፍያዎች ላይ ተቀንሶ የሚቀረው ታክስ በቅድመ ክፍያ ግዜ እና በከፊል ከሚፈፀሙ ክፍያዎች ላይም ይቀነሳል፡፡
- ክፍያው የተፈፀመው በዶላር ከሆነ በባንክ በኩል ወደ ብር ተቀይሮ በተቀየረበት መጠን ላይ ታክስ ይሰበሰባል፡፡

በገቨው ተይዞ ስለሚከፈል...

- ሜጋ ፕሮጀክቶችን የሚያከናውኑ የመንግስት የልማት ድረጅት ከሚፈፅሙት ክፍያ ላይ ታክስ ቀንሰው የሚያስቀሩት የአገልግሎት ዋጋ ነው ተብሎ በሚወሰደው 50% ላይ ብቻ ነው።

- የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከውጭ አገር በብድር ባገኙት ገንዘብ ለሚከናወን ፕሮጀክት ክፍያ የሚፈፀመው በአበዳሪው አካል ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ አይደረግም።

- በቴሌ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ በገቨው አይያዝም።

በቀጥታ በገዢው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት

- የተመዘገበ ሰው ቢሆንም ባይሆንም አቅርቦቱ የተከናወነው ከኢትዮጵያ ውጪ ባለ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት በሚሠራ ድርጅት አማካኝነት ታክስ የሚከፈልበትን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በምያከናውን ሰው አማካኝነት ከሆነ፣
- አቅርቦቱ የተሰጠው ለተመዘገበ ሰው፣ ለመንግስት ተቋም ወይም ከፍተኛ ግብይት ላለው ያልተመዘገበ ሰው ከሆነ እና
- አቅርቦቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ የንግድ ሥራ ቦታ ቢሰጥ ኖሮ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

ታክሱ ተቀናሽ የሚደረግበት የግብይት ዋጋ

- ወኪሉ ከብር 200,000 ብር በላይ ዋጋ ያለው ዕቃ /አገልግሎት ሲገዛ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገበ ግብር ከፋይ መሆን አለበት።
- ለታክስ ከፋዩ በአንድ ጊዜ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ከ 20,000 በላይ ሲሆን ወኪሉ የታክሱን 50% ቀንሶ ማስቀረት አለበት።
- ነገር ግን በአንድ ጊዜ የሚከፈለው ክፍያ 20,000 እና በታች ከሆነ የታክሱን ሂሳብ ጨምሮ ለታክስ ከፋዩ መክፈል አለበት።

የወኪሉ ግዴታ

- ታክሱን ቀንሶ ለማስቀረት ውክልና የተሰጠውቷን ሰርቲፊኬት መያዝ አለበት።
- በእያንዳንዱ ታክስ በሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል ከሚገባው ታክስ ላይ 50% ቀንሶ የመያዝ፤
- ቀንሶ በሚይዘው ታክስ መጠን ልክ በገዥው ተይዞ የሚከፈል ለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የመስጠት
- በሚፈፅመው ክፍያ ከዕቃ/ከአገልግሎት አቅራቢው የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የመቀበል

- ወኪሉ ታክሱን በትክክል ቀንሶ ያላስቀረ እንደሆነ/ የቀነሰውን ታክስ ለገቢ መስሪያ ቤቱ ገቢ ያላደረገ እንደሆነ ወኪሉ የሚከፍለውን ታክስ ወለድ እና መቀጫውን ጨምሮ እንድከፍል ይደረጋል።
- ወኪሉ የዕቃ/አገልግሎት አቅራቢው ደረሰኝ በሰጠበት ወር በገዥው ተይዞ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ካልሰጠው መስጠት ከነበረበት እና እስከ ሰጠበት ባለው ጊዜ ውስጥ ወለድና ለዘገየበት ቅጣት እንድከፍል

የወኪሉ ግዴታ...

- ቀንሶ የያዘውን ታክስ ወሩ በተጠናቀቀ በቀጣዩ ወር በ30 ቀን ውስጥ ለገቢ መስሪያ ቤቱ ገቢ ማድረግ
- ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ጋር ተያይዞ ክፍያ የተፈፀመለትን አካል ዝርዝር የታክስ መረጃዎችን ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው ቅፅ ሞልቶ ማቅረብ
- በግብይት የሚከፈለው ታክስ ለአቅራቢው የሚከፈል/ተቀንሶ የተያዘ ታክስ ከሌለ ወሩ ከተጠናቀቀ በቀጣይ 30 ቀናት ውስጥ ለገቢ መስሪያ ቤቱ በደብዳቤ ማረጋገጥ አለበት፡፡

5. የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ማሳወቅ፤ ስረዛ ፤ አስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች

ማሳወቅ

- ማናቸውም የተመዘገበ ሰው የእያንዳንዱን የሒሣብ ጊዜ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ የሒሣብ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኋላ ቀጥሎ ባለው ወር የመጨረሻ ቀን ድረስ ማቅረብ አለበት።
- ማናቸውም የተመዘገበ ሰው በሒሣብ ጊዜው ውስጥ ተከፋይ የሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ቢኖረውም ባይኖረውም የሒሣብ ጊዜውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

5.2. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ስረዛ

- የሚያከናውነው ዓመታዊ ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ዋጋ የመመዝገብ ግዴታን ከሚያስከትለው የገንዘብ መጠን ሲወርድ ምዝገባው ከተከናወነበት ቀን ጀምሮ ከሚቆጠር የ2 ዓመት ጊዜ በኋላ
- በስህተት የተመዘገበ ሰው ከተመዘገበበት ቀን በኋላ የመጀመሪያውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ማስታወቂያ ማቅረብ ከሚገባው ቀን በፊት የይሰረዝልኝ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
- ምዝገባው በተሰረዘ ጊዜ በእጁ የሚገኙትን የንግድ ዕቃዎች እና የካፒታል እቃዎች አቅርቦት እንዳከናወነ ይቆጠራል፡፡

ስረዛ

- ምዝገባ በሚሰረዝበት ጊዜ በእጁ ለሚገኙ የካፒታል ዕቃዎች ከዚህ በታች በተመለከተው ቀመር መሠረት የውጤት ታክስ እንደተቀበለ ይቆጠራል፡፡

ሀ X ለ/ሐ

- ሀ) ማለት የተመዘገበው ሰው የካፒታል ዕቃዎችን በገዛበት ጊዜ ያገኘው የግብአት ታክስ ተቀናሽ፣
- ለ) ማለት በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሚወሰን የተመዘገበው ሰው ምዝገባ በተሰረዘበት ጊዜ የካፒታል ዕቃዎች ያላቸው የተጣራ የመዝገብ ዋጋ፣ እና
- ሐ) ማለት ለካፒታል ዕቃዎቹ የተደረገው የመጀመሪያው ወጪ፡፡

➢ የታክሱ ባለስልጣን የተመዘገበው ሰው ምዝገባው ከጸናበት ቀን አንስቶ ለተከታታይ

❖ ለስድስት (6) ወር ምንም አይነት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ያለማከናወኑን ካረጋገጠ ምዝገባው ከጸናበት ቀን አንስቶ እንዲሰረዝ ሊወስን ይችላል።

❖ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የምስክር ወረቀትን ለመሠረዝ የተሰጠ ውሳኔ ተፈፃሚ የሚሆነው የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ማከናወን ካቆመበት የሒሣብ ጊዜ የመጨረሻ ቀን ወይም በስረዛው ውሳኔ ማስታወቂያ ከተገለፀው ቀን ጀምሮ ይሆናል።

❖ የተመዘገበ ሰው ታክስ የሚከፈልበትን እንቅስቃሴ ሲያቆም የሚሰጠው ማስታወቂያ፣

- ✓ በተፈቀደው ቅጽ በመጠቀም የሚቀርብ፣
- ✓ የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ማከናወን ያቆመበትን ቀን፣
- ✓ ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ማከናወን ካቆመበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር 12 ወራት ውስጥ የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበት አቅርቦት ለማከናወን ፍላጐት ያለው ወይም የሌለው መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን እና የተመዘገበው ሰው ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት ካቆመበት ቀን አንስቶ በ7 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

ምዝገባን ስለማገድ

- ታክስ የሚከፈልበትን አቅርቦት የማከናወኑን ተግባር በጊዜያዊነት ያቋረጠ የተመዘገበ ሰው የጸደቀውን ቅጽ በመጠቀም ምዝገባው ለ12 ወራት እንዲታገድለት ሊያመለክት ይችላል፡፡
- ምዝገባው የታገደበት ሰው የምዝገባው መታገድ በጸናበት ቀን ወደፊት የተሸጋገረ ክሬዲት ሊደረግ የሚችል ሂሳብ ያለው እንደሆነ ክሬዲት ሊደረግ የሚገባው ሂሳብ እገዳው እስከሚሻር ድረስ እንዲቆይ ሆኖ እገዳው ሲነሳ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
- ምዝገባው የታገደበት ሰው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ማከናወኑን የማይቀጥል ከሆነ ምዝገባው ታግዶ ባለበት በማናቸውም ጊዜ ምዝገባው እንዲሰረዝለት ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

- የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የታደበት ሰው ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች አቅርቦት ለመቀጠል ከፈለገ እገዳው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ውስጥ ቢያንስ ከ15 ቀን በፊት ለታክሱ ባለስልጣን ጥያቄ ማቅረብ አለበት።
- ምዝገባ የታገደበት ሰው ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች አቅርቦት ማከናወን ለመቀጠል ከፈለገ እገዳው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ውስጥ ቢያንስ ከ15 ቀን በፊት ለታክሱ ባለስልጣን ማመልከቻ ካላቀረበ የእገዳው ጊዜ እንደተጠናቀቀ ምዝገባው ይሰረዛል።

ክፍል ስድስት

6. ከተጨማሪ ዕሴት ታክስ ጋር የተያያዙ አስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች

6.2. አስተዳደራዊ ቅጣት

- ለጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ያለበት ሰው ሳይመዘገብ የቀረ እንደሆነ፤ መመዝገብ ከነበረበት ቀን ጀምሮ ለመመዝገብ እስካመለከተበት ወይም በባለስልጣኑ አነሳሽነት እስከተመዘገበበት ቀን ድረስ ላለው ለእያንዳንዱ ወር ወይም ከወሩ ከፊል ለሆነው ጊዜ ብር 2 ሽህ (ሁለት ሽህ ብር) ቅጣት ይከፍላል።
- ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ ሊከፈል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለማሳነስ ወይም በግብቱ ላይ ተመላሽ የሚደረገውን የታክስ መጠን ለመጨመር በማሰብ ትክክለኛ ያልሆነ የታክስ ደረሰኝ የሰጠ እንደሆነ ብር 50 ሽህ (ሃምሳሽህ ብር) ቅጣት ይከፍላል።

አስተዳደራዊ ቅጣት...

- ደረሰኝ መስጠት ሲገባው ያልሰጠ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ለገዥ ባልሰጠው ለእያንዳንዱ ደረሰኝ ብር 50 ሺህ (ሃምሳ ሺህ) ቅጣት ይከፍላል።
- በታክስ ማስታወቂያ የተገለጸው የታክስ መጠን ታክስከፋዩ ሊከፍል ከሚገባው ትክክለኛ የታክስ መጠን ያነሰ እንደሆነ (“የታክስ ጉድለት” ልዩነት እና የልዩነቱን መጠን በ10% ይቀጣል።ይህንኑ ከደጋገመ ልዩነቱን በ 30-50 % ከፍ ይላል።

6.3. የወንጀል ቅጣቶች

- ባለስልጣኑን ለማጭበርበር በማሰብ ያለአግባብ ተመላሽ ወይም ማካካሻ የጠየቀ ሰው ብር 50 ሺህ (ሃምሳ ሺህ ብር) የገንዘብ ቅጣት እና ከአምስት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል። የሚጣለው ቅጣት ታክስ ከፋዩ ተመላሽ የተደረገለትን ታክስ መልሶ ከመክፈል ግዴታ ነፃ ሊያደርገው አይችልም።
- ለተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይመዘገብ የታክስ ደረሰኝ የሰጠ ሰው ብር 200 መቶ ሺህ (ሁለት መቶ ሺህ ብር) የገንዘብ ቅጣት እና ከሰባት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

የወንጀል ቅጣቶች...

- ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ማንኛውም ሰው፤

ሀ/ በተ.እ.ታ አዋጅ መሰረት የታክስ ዴቢት ወይም ክሬዲት ማስታወሻ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ

ለ/ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ከተፈቀደው ውጭ የታክስ ዴቢት ወይም ክሬዲት ማስታወሻ የሰጠ እንደሆነ፤ብር 10 ሺህ (አስር ሺህ) የገንዘብ ቅጣት እና በአንድ ዓመት ቀላል ዕስራት ይቀጣል፡፡

የወንጀል ቅጣቶች…

- ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ የተጭበረበሩ ደረሰኞችን ያዘጋጀ፣ ያተመ፣ የሸጠወይም ያሰራጨ፤ወይም

ለ/ የታክስ ዕዳውን ለመቀነስ ወይም ተመላሻ ለመጠየቅ የተጭበረበሩ ደረሰኞችን የተጠቀመ እንደሆነ፤ብር100 ሺ. የገንዘብ ቅጣት እና ከ7-10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

የወንጀል ቅጣቶች…

- ሀሰተኛ ደረሰኞችን፣ ለማዘጋጀት/ለማተም የሚያገለግል ማሽን፣ መሳሪያ፣ ወይም ሶፍት ዌር የያዘ፣ የሸጠ፣ ያከራየ፣ ወይም በሌላ መንገድ ያቀረበ ማንኛውም ሰው ብር 200ሺ የገንዘብ ቅጣት እና ከ 10-15 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል።
- ሀሰተኛ ደረሰኞችን የያዘ፣ ያስቀመጠ፣ ለሽያጭ ያመቻቸ፣ ወይም ሀሰተኛ ደረሰኞች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደረገ ሰው ከ3-5 ዓመት በሚደረስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡
- ግብይት ሳይፈጸም ደረሰኝ የሰጠ ወይም የተቀበለ ሰው ከብር 100 ሺ እስከ ብር 200 ሺ ቅጣት እናከ 7-10 ዓመት በሚያደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

የወንጀል ቅጣቶች...

- ማንኛውም ሰው ታክስን ለመሰወር በማሰብ ገቢውን የደበቀ፣የታክስ ማስታወቂያውን ያላቀረበ ወይም ታክሱን ያልከፈለ እንደሆነ ከብር 100-200 ሺ. ቅጣት እና ከ3-5 ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡
- ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ታክስን ቀንሶ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት የተጣለበት ሰው ታክስን ለመሰወር በማሰብ ቀንሶ የያዘውን ታክስ ለመንግስት ያላስተላለፈ ከሆነ ከ3-5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡

አመሰግናለሁ